## ሥነ ምግባር

**የምዕራፉ ዓላማዎች፡-**

**ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-**

- የመልካም ሥነ ምግባር መመሪያን ትገልጻላችሁ፡፡
- መምህሩ የሚነያቡላችሁን በማዳመጥ ጥቄዎችን ትመላሳላችሁ፡፡
- የቃላትን ፍቺ እና ተዛማጅ ቃላትን ትለያላችሁ፡፡
- ቃላትን በመጠቀም ነጠላ አረፍተ ነገር ትመሰርታላችሁ፡፡
- ብዙና ነጠላ ቁጥሮችን ትለያላችሁ፡፡
- ቃላትን በቅደም ተከተል ታደራጃላችሁ፡፡


## ክፍለ ትምህርት አንድ

**የክፍለ ትምህርቱ ዓላማ፡- አዳምጦ መመለስ**

**ተማሪዎች፡-** መምህር/ት የሚያነቡላችሁን ምንባብ አዳምጣችሁ ለምትጠየቁት ጥያቄ መልስ ትሰጣላችሁ፡፡

**ትእዛዝ**

ተማሪዎች፡- መምህር/ት **"ክብር ስጡ!"** የሚለውን ምንባብ ከመምህሩ መምሪያ ሲያነቡላችሁ በጥሞና አዳምጡ፡፡



**መልመጃ**

ሀ. ተማሪዎች በሥዕሉ ላይ ምን ይታያችኋል?

ለ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ትመልሳላችሁ

1. ፍቅርተ ለጀማል ያሳየችው ምንድነው?
2. አዛውንቱ ምን ይዘዋል?
3. ፍቅርተና ጀማል ምን አደረጉ?

# ክፍለ ትምህርት ሁለት

**የክፍለ ትምህርቱ ዓላማ፡- የቃላትን ፍቺ መለየት**

ተማሪዎች ከዚህ ክፍለ ትምህርት በኋላ የተለያዩ ቃላት ፍቺን ትለያላችሁ፡፡

**ትእዛዝ** ፩. ከዚህ በታች ለቀረቡ ቃላት ፍቻቸውን ተናገሩ፡፡

ሀ. ተሸከሙ        መ. አዘኑ

ለ. አሳየች        ሠ. ረዳ

ሐ. ተቀበለ

**መልመጃ**

ከዚህ በታች ያሉትን ቃላት በምሳሌው መሠረት ጻፉ፡፡

ምሳሌ፡-

ሰጠ - ቸረ፣ ለገሰ

ሀ. ተቀበለ ……………………

ለ. ታመመ……………………

ሐ. አዘነ………………………

መ. ታዘዘ………………………

ሠ. ያዘ…………………………

ረ. ተቀመጠ……………………

ሰ. መለሰ………………………

## ክፍለ ትምህርት ሦስት

**የክፍለ ትምህርቱ ዓላማ፡- ነጠላ ዓረፍተ ነገርን መመሥረት**

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ ቃላትን በመጠቀም ነጠላ ዓረፍተ ነገሮችን ትመሠርታላችሁ፡፡

**ትእዛዝ ፩.**

ተማሪዎች በመምህራችሁ የሚሰጣችሁን መመሪያ ተግብሩ፡፡

**ትእዛዝ ፪.**

ከዚህ በታች የተሰጡትን ቃላት በመጠቀም የተመሰረቱ ነጠላ ዓረፍተ ነገሮችን አንብቡ፡፡

| | |
|---|---|
| ሀ. ሸለመ | ርእሰ መምህሩ ጎበዟን ተማሪ ሸለመ፡፡ |
| ለ. መከረ | አባት ልጁን መከረ፡፡ |
| ሐ. ታከመ | ህመምተኛው ታከመ፡፡ |
| መ. ተረዳች | ትምህርቱን ተረዳች፡፡ |
| ሠ. ታጨደ | ጤፉ ታጨደ፡፡ |

**መልመጃ**

ከላይ በተማራችሁት መሠረት በሚቀጥሉት ቃላት ዓረፍተ ነገሮችን መሥርቱ፡፡

| | |
|---|---|
| ፩. ቀቀለች | ፬. ተገዛች |
| ፪. ታመመ | ፫. ተከሰ |

፫. ቀለጠ

## ክፍለ ትምህርት አራት

**የክፍለ ትምህርቱ ዓላማ፡- ነጠላና ብዙ ቁጥርን መለየት፣**

**ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ ነጠላ እና ብዙ ቁጥሮችን በመለየት ዓረፍተ ነገር ትመሠርታላችሁ።**




**ትዕዛዝ ፩.**

ተማሪዎች በአካባቢያቸው ያሉ ነገሮችን በነጠላና በብዙ ቁጥሮች እየጠራችሁ ተለማመዱ።


| ነጠላ | ብዙ |
|---|---|
| ምሳሌ፡- ሰው - ሰው መጣ። | ሰዎች - ሰዎች መጡ። |
| በር- በር ተከፈተ። | በሮች - በሮች ተከፈቱ። |
| ሀገር - ሀገር ተከበረ። | ሀገሮች - ሀገሮች ተከበሩ። |

**መልመጃ.**

ቀጥሎ የቀረቡ ሥዕሎችን በመመልከት ብዛታቸውን የሚገልጽ ዓረፍተ ነገር መሥርቱ። ምሳሌ፡- አራት መኪናዎች አሉ።







## ክፍለ ትምህርት አምስት

የክፍለ ትምህርቱ **ዓላማ፡-** መልካምና መጥፎ ሥነ ምግባርን ማወቅ፤

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች የመልካም ሥነ ምግባር እና የመጥፎ ሥነ ምግባር ልዩነቶችን አውቃችሁ ትተገብራላችሁ፡፡

**ትዕዛዝ ፩.** ተማሪዎች መምህራችሁ የሚነግሯችሁን የመልካምና የመጥፎ ሥነ ምግባር መገለጫዎች አዳምጡ

**ለምሳሌ፡-** መታዘዝ መልካም ሥነ ምግባር ሲሆን ያለመታዘዝ ደግሞ የመጥፎ ሥነ ምግባር መገለጫ ነው፡፡

**ትዕዛዝ ፪.**ተማሪዎች ከታች የተሰጧችሁን ቃላት መልካም ሥነ ምግባር እና መጥፎ ሥነ ምግባር በማለት በምሳሌው መሠረት መድቧቸው፡፡

| | | |
|---|---|---|
| መስረቅ | እውነተኛነት | መዋሸት |
| ግላዊነት | አለመታዘዝ | ታማኝነት |
| መምከር | አክብሮት | መሳደብ |
| ሀቀኝነት | ማጭበርበር | መታገስ |

**ምሳሌ፡-**

| ጥሩ ሥነ-ምግባሮች | | መጥፎ ሥነ-ምግባሮች | |
|---|---|---|---|
| እውነት መናገር | | መስረቅ | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |

# ክፍለ ትምህርት ስድስት

**የክፍለ ትምህርቱ ዓላማ፡- የተዘበራረቁ ቃላትን በሥርዓት ማስቀመጥ፣**

ከዚህ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች የቃላትን ቅደም ተከተል በማስተካከል ዐረፍተ ነገሮችን ትፅፋላችሁ፡፡

**ለምሳሌ፡-** መምህራንን እወዳቸዋለሁ በጣም፡፡ መምህራንን በጣም እወዳቸዋለሁ፡፡

## ትዕዛዝ

ከላይ በተሠጣችሁ ምሳሌ መሠረት ተዘበራርቀው የተቀመጡ ቃላትን በቅደም ተከተል ጻፉ፡፡

1. አዛውንቱን ረዳኂቸው በስራ፡፡ ____________________
2. ርዕስ መምህራችን ሰበሰቡን ዛሬ፡፡ ____________________
3. ተሸከሙ እቃ አባባ፡፡ ____________________
4. አባባን አገዝኳቸው ሮጬ፡፡ ____________________

**መልመጃ**

የሚከተሉትን ቃላት በነጠላ ቁጥር ጻፉ

**ምሳሌ፡-** ዝሆኖች - ዝሆን

ሀ.ዘመዶች………. ሐ. ልጆች……………

ለ.ዝማሬዎች…… መ. ዓይነቶች …….

# ክፍለ ትምህርት ሰባት

**የክፍለ ትምህርቱ ዓላማ፡- አብሮነትን ማጎልበት፣**

**ተማሪዎች፡-** ከዚህ ትምህርት በኋላ ስለጉርብትና በቡድን በመሆን ነጠላ ዓረፍተ ነገሮችን ትመሠርታላችሁ፡፡

**ምንባብ**

አብሮ መኖር የሰው ልጆችን ማኅበራዊ ህይወት ያጠናክራል፡፡ ማኅበራዊ ህይወት የሚጎለብተው በሰዎች መካከል መከባበር፣ መቻቻልና መተማመን ሲኖር ነው፡፡ በጥሩ ጉርብትና የሚኖሩ ሰዎች እነዚህን ፀጋዎች ይጋራሉ፡፡ የመኖሪያ አካባቢያቸውም ምቹና ተናፋቂ ይሆናል፡፡ በጉርብትና የሚኖሩ ሰዎች በበዓላት ቀናት የተጣሉ ወገኖችን ያስታርቃሉ፤ ሕሙማንንም በጋራ ይጠይቃሉ፡፡

የሚከተሉትን ጥያቄዎችን ምንባቡን መሠረት በማድረግ በቃላችሁ መልሱ፡፡

ሀ. በጥሩ ጉርብትና የሚኖሩ ሰዎች ምን ምን ነገሮች ይጋራሉ?

ለ. ማኅበራዊነት የሚጎለብተው በሰዎች መካከል ምን ሲኖር ነው?

ሐ. ጥሩ ጎረቤቶች ለበዓል ቀን ምን ያደርጋሉ?

መ. የጥሩና መጥፎ ጎረቤት ልዩነቶችን ዘርዝሩ፡፡

# ክፍለ ትምህርት ስምንት

የክፍለ ትምህርቱ **ዓላማ፡-** የመልካም ሥነ ምግባር መገለጫዎችን መገንዘብ፣

ከዕለቱ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡- የሥነ ምግባር መገለጫዎችን ይዘረዝራሉ፤ ይተግብራሉም፡፡

**ተማሪዎች፡-** መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን የመልካም ሥነ ምግባር መርሆች በሚል የቀረበውን ምንባብ በጽሞና ተከታተሉ፡፡

## የመልካም ሥነ ምግባር መገለጫዎች

የሥነምግባር መገለጫዎች የሚባሉት ሀቀኝነት፣ ቅንነት፣ ታማኝነት፣ ግልጸኝነት፣ ተጠያቂነት፣ አለማዳላት፣ ምሥጢር ጠባቂነት፣ ሕግን ማክበርና አርዓያ መሆን የሚሉትን መርሆዎች ያካትታል፡፡ ሀቀኝነት ማለት ሰዎችን ማክበር፣ ታማኝነትን በአግባቡ መወጣት፣ አደራን ተቀብሎ በአግባቡ መያዝ፣ የሰውን ንብረት ካልተፈቀደ በስተቀር አለመንካት፣ አለመስረቅና የመሳሰሉትን ድርጊቶች የሚያካትት ነው፡፡ በተጨማሪም አለመሳደብ፣ ለሌሎች ቅድሚያ መስጠት፣ መታዘዝ፣ ጓደኛን መውደድ እና ከራስ ይልቅ ለሰዎች ማሰብን ይጠይቃል፡፡

**መልመጃ፡- ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎች**

1. መልካም ሥነ ምግባር ከሚባሉት ውስጥ አንዱን ጥቀሱ፡፡

   ………………..

2. የሰውን ንብረት ሳይፈቀድ መንካት ያስፈልጋል?

   …………………………

3. ሌሎች የሥነ-መግባር መርሆችን ጥቀሱ፡፡ …………………………

**በሚከተሉት ከሥነ ምግባር ጋር በተያያዙ ቃላት ምሳሌውን መሠረት አድርጋችሁ ዐረፍተ ነገሮችን ሥሩ፡፡**

**ምሳሌ፡- መተባበር - መተባበር ድህነትን ይቀንሳል፡፡**

ሀ. መተጋገዝ ……………………………………….

ለ. መከባበር ……………………………….

ሐ. መተማመን …………………………………

መ. መቻቻል ………………………………..

ሠ. መታዘዝ ……………………………….

## ክፍለ ትምህርት ዘጠኝ


**የዕለቱ ትምህርት ዓላማ፡- የሥነ ምግባር መገለጫዎችን ማወቅና መጻፍ፣**

**ከዚህ ትምህርት በኋላ፡- ተማሪዎች የሥነ ምግባር መገለጫዎችን በመዘርዘር ትጽፋላችሁ።**

**ትዕዛዝ፤**ተማሪዎች ስለ መልካም ሥነ ምግባር ምንነት ተወያዩ።

"ታላላቆቻችሁን አክብሩ" ማለት በዕድሜ የሚበልጡንን ሰዎች ተገቢ እክብሮት መስጠት ማለት ነው፤ ተገቢ አክብሮት ደግሞ በብዙ መንገድ ይገለፃል። **ለምሳሌ** አዛውንቶች መንገድ ሲያቋርጡ ደግፈን ማሳለፍ፣ ዕቃ ከተሸከሙ ተቀብለን መሸኘት፣ ..... በአጠቃላይ ከራሳችን ይልቅ ለሌሎች ቅድሚያ መስጠት ነው።

**መልመጃ፡-** ቀጥሎ የቀረበውን ሥዕል ተመልከቱና ድርጊቱን በጹሑፍ ግለጹ።



፩. ከላይ የሚታየውን ሥዕል በጽሑፍ ግለጹ ..............................

፪. አዛውንቱ ምን እያደረጉ ነው? .......................................

## ክፍለ ትምህርት አሥር

**የክፍለ ትምህርቱ ዓላማ፡- ሐሳብን በጹሑፍ መግለጽ**

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡- የመልካም ሥነ ምግባር መገለጫዎችን በጽሑፍ ይዘርዝራሉ፡፡

**ትእዛዝ ፩.** የሥነ ምግባር መገለጫዎችን በየተራ በመነሳት በጋደኞቻቸው እንዲናገሩ ያድርጉ፡፡

**ትእዛዝ ፪.** መምህር/ት የሚነግሯችሁን የሥነ ምግባር መገለጫዎችን በማዳመጥ በክፍል ውስጥ ተወያዩ፤ በመቀጠልም በምሳሌው መሠረት የመጀመሪያ ፊደል ነጥላችሁ ጻፉ፡፡

**ምሳሌ** ፡ ተሰጠ   ተ - ሰጠ

**መልመጃ አንድ**

፩. ተወደደ ……………..   ፫. አስመከረ ……………....

፪. አስቀጣ ………………   ፬. ተሰደበ ………………

**መልመጃ ሁለት፡-** እስካሁን የተማራችኋቸውን የሥነ ምግባር መገለጫዎች በዝርዝር ጻፉ፡፡

**ምሳሌ፡-**

1. **ሀቀኝነት**
2. **ታማኝነት**

# ምዕራፍ ስምንት

## የአመጋገብ ሥርዓት

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ✓ መሠረታዊ ቃላትን ትናገራላችሁ፡፡
- ✓ በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልስ ትሰጣላችሁ፡፡
- ✓ ቀለማትንትለያላችሁ፡፡
- ✓ አረፍተ ነገሮችንትጽፋላችሁ፡፡
- ✓ የመመገቢያ እቃዎችን እና አገልግሎታቸውን ትገልጻላችሁ፡፡
- ✓ ሥርዐተ ነጥቦችን በትክክ ትገልጻላችሁ ትጠቀማላችሁ፡፡
- ✓ ፊደላትን በክፍት ቦታዎች በመሙላት ቃላትን ትመሠርታላችሁ፡፡
- ✓ በሚሰጣቸው ምሳሌ መሠረት ቃላትን በየምድባቸው ታስቀምጣላችሁ፡፡
- ✓ የፊደላትን ቦታ በማቀያየር ወይም በመቀነስ ቃላትን ትመሠርታላችሁ፡፡
- ✓ ፊደላትን በማጣመር ቃላትን ትጽፋላችሁ፡፡
- ✓ በተሰጣቸው ቃላት ዓረፍተ ነገሮችን ትመሠርታላችሁ፡፡

# ክፍለ ትምህርት አንድ

## ክፍለ ትምህርቱ ዓላማ፡- አዳምጦ መመለስ

ከዚህ ዕለት ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ምንባቡን በማዳመጥ ትመልሳላችሁ፡፡

**ትዕዛዝ፩.** ተማሪዎች ስለተመጣጣኝ ምግቦች አስፈላጊነት ተናገሩ፡፡

### የተመጣጠኑ ምግቦችና አስፈላጊነታቸው

የተመጣጠኑ ምግቦች በሦስት ይመደባሉ፡፡ አንደኛው ገንቢ ምግብ በመባል ይታወቃሉ፡፡ በዚህ ውስጥ እንቁላል፣ አሳ፣ ሥጋ፣ አይብ፣ አተር፣ ባቄላና የመሳሰሉት ይካተታሉ፡፡ ሁለተኛ፣ ሀይልና ሙቀት ሰጪ ምግብ ነው፡፡ እንደ ጮማ ሥጋ፣ ቅቤ፣ ወተት፣ ጥራጥሬ፣ ዳቦ፣ ማር፣ ስኳርና የመሳሰሉትን አካቶ ይይዛል፡፡ ሦስተኛ ደግሞ ከበሽታ ተከላካይ ምግቦችን የያዘ ነው፡፡

*ተማሪዎች ከበሽታ የሚከላከሉ ምግቦች ምን ምን ይመስሏችኋል?*

በሽታ ተከላካይ ምግቦች ብርቱካን፣ ሎሚ፣ ፓፓያ፣ ሙዝ እና ትርንጎ ወዘተ ናቸው፡፡ ማንኛውም ሰው በየቀኑ ከሁሉም የምግብ ዓይነቶች በመጠኑ ካገኘ ጠንካራና ጤናማ ይሆናል፡፡

**፪.** ከዚህ በታች ከምንባቡ የተወጣጡ ጥያቄዎች ቀርበዋል በምንባቡ መሠረት መልሱ፡፡

፩. ተመጣጣኝ ምግቦች በስንት ይከፈላሉ? ..............................

፪.ገንቢ ምግቦች የሚባሉትን መልሱ? ..............................


፫. በሽታን ተከላካይ ምግቦችን ግለጹ፡፡ ..............................

## ክፍለ ትምህርት ሁለት

**የክፍለ ትምህርቱ ዓላማ፡- የተመጣጠኑ ምግቦችን በዓይነት መመደብ፣**

ከዚህ ክፍለ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፣ ስለ ተመጣጠኑ የምግብ ዓይነቶች ያውቃሉ፡፡

ቀጥሎ የቀረቡትን የምግብ አይነቶች የያዘውን ሥዕል ከመግለጫወቻቸው ጋር አዛምዱ፡፡



ሀ. በሽታ ተከላካይ ምግቦች፡- ....................................................................

ለ. ገንቢ ምግቦች፡- ....................................................................

# ክፍለ ትምህርት ሦስት


## የክፍለ ትምህርቱ ዓላማ፡- ቀለማትን መለየት


ከዚህ ክፍለ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፣ ስለ ቀለማት ዓይነቶች ታውቃላችሁ፡፡


የትራፊክ መብራት ማለት ተሽከርካሪዎች በተራና በስርዓት እንዲተላለፉ በመስቀልኛ መንገድ ላይ የሚተከል ምልክት ነው ፡፡

በዚሁ መሰረት በጉዞ ላይ ያሉ ተሽከርካሪዎች ቀይ መብራት ሲበራ ይቆማሉ ቢጫው ሲበራ ደግሞ ለመንቀሳቀስ ይዘጋጃሉ፤አረንጓዴ ሲበራ ወደፊት ይንቀሳቀሳሉ፡፡


፩ 

፪ 

፫ 

፬ 

፭ 

፮ 

**መልመጃ፡-**

ሀ. ከላይ የቀረቡትን ሥዕሎች በመመልከት ቀለማቱን በጹሑፍ ግለጹ

፩.............................	፬.............................

፪.................................	፭.............................

፫.................................	፮.................................

ለ. የትራፊክ ምልክቶችን ግለጹ ........................................

## ትምህርት አራት

### የክፍል ትምህርቱ ዓላማ፡- ቃላትን በማቀናጀት ዓረፍተ ነገር መጻፍ፣

፩. ቀጥሎ በቀረበው ሥዕል ምን አያችሁ?

**ትዕዛዝ ፪.** በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተ ነገር ሥሩባቸው፡፡

፩. ባቄላ

፪. ወተት

፫. አሳ

፬. ፓፓያ

፭. አትክልት

**መልመጃ፡-** ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በምሳሌው መሠረት በዓረፍተ ነገር ግለጹ፡፡

፩. <u>**ምሳሌ**፡- </u>ጤናማ አመጋገብ ለምን ይጠቅማል?

መልስ - ጤናማ አመጋገብ በሽታን ለመከላከል ይጠቅማል፡፡

፪. በስለው የሚበሉ ምግቦችን በጥሬያቸው ብንመገብ ምን እንሆናለን?

፫. ሥጋ ከየትኛው የምግብ ዓይነት ይመደባል?

፬. ብርቱካን መመገብ ምን ምን ጥቅሞችን እናገኛለን?

፭. የሰላጣ ጥቅምስ ምንድን ነው?

# ክፍለ ትምህርት አምስት

**የክፍለ ትምህርቱ ዓላማ፡-** የምግብ ማቅረቢያና ማብሰያ ዕቃዎችን መግለጽ፣

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፣ የምግብና የመጠጥ ቁሶችን አገልግሎት ትለያላችሁ፡፡

**፩.** እነዚህ ሥዕሎች ለምን ይጠቅማሉ?





**፪.** ሥዕሉን ተመልክታችሁ የቁሶቹን ስም ጻፍ፡፡

፩.



፪.



፫.



፬



፭



፮



**መልመጃ፡-** የምግብና የመጠጥ ቁሶችን አገልግሎት በምሳሌው መሠረት ግለጹ፡፡

፩. ድስት፡- ዳንቺሌ በሸክላ ድስት ወጥ ሰራች፡፡

፪. ቢለዋ፡- ..................................................................

፫. ማንኪያ፡- ..................................................................

፬. ማጥለያ፡- ..................................................................

፭. ሳህን፡- ..................................................................

## ክፍለ ትምህርት ስድስት

### የዕለቱ ትምህርት ዓላማ፡- የሥርዓተ ነጥቦችን አገልግሎት ማወቅ፣

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ ሥርዓተ ነጥብን በተገቢው ቦታ በማስገባት ትገለገላላችሁ፡፡

**ትዕዛዝ.** ቀጥሎ በቀረበው ምንባብ ውስጥ ያሉትን ሥርዓተ ነጥቦች ለይታችሁ አውጡ፡፡

እናቴ ሁልጊዜ 12፡ 30 የመነሣት ልምድ አላት፡፡ እኔም እናቴን ተከትዬ በመነሳት “ምን እየሰራሽ ነው?” ብዬ እጠይቃለሁ፡፡ እናቴም ቁሶቹን እያነሳች፣ “ጎድጓዳ ሳህኖችና የሸክላ ድስቶች ለሥጋ፣ ለአትክልት፣ ለወጥ ማቅረቢያነት ያገለግላሉ፡፡ ሹካና ማንኪያ ደግሞ ለፓስታና ለመኮሮኒ እንዲሁም ለአትክልት መመገቢያ ይጠቅማሉ፡፡ ለመጠጫ ደግሞ ሲኒዎችን፣ ብርጭቆዎችንና ኩባያዎችን መጠቀም እንችላለን፡፡” በማለት ነገረችኝ፡፡

**መልመጃ፡-** በምንባቡ ውስጥ የተጠቀሱትን ሦስት ስርዓተ ነጥቦች ለይታችሁ አውጡ፡፡ ለምሳሌ፡- ( “ ” ) የጥቅስ ምልክት

፩. ------------------------------

፪.--------------------------------

፫. ------------------------------

## ክፍለ ትምህርት ሰባት

**የዕለቱ ትምህርት ዓላማ፡- ቃላትን መመሥረት፣**

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፣ በክፍት ቦታዎች ተገቢ ፊደላትን በመሙላት ቃላትን ትመሠርታላችሁ፡፡

**ትዕዛዝ ፩.** “ተ”ን በመነጠል ቃላቱን ለዩ፡፡ ምሳሌ፡- ተወደደ - ወደደ

ተበላ - በላ

፩. ተነገረ ------------ ፪. ተመከረ - --------------- ፫. ተሰበረ --------

**ትዕዛዝ ፪.** የተዘለሉትን ፊደላት ከሳጥን ውስጥ በመምረጥ አሟልታችሁ ቃል መሥርቱ፡፡

ባ - ት - ን ም - ሳ -
ሹ - ብ- ር- ማ

፩. ኩ -------ያ

፭. ------ ኒ

፪. ድስ ------

፮. ------- ካ

፫. ማ------- ኪያ

፯. ------ ጭቆ

፬. -------- ጣድ

፰. ------- ማሰያ

**መልመጃ፡-** ቀጥሎ በቀረቡት ቃላት በምሳሌው መሠረት ዓረፍተ ነገር መሥርቱ፡፡

፩. ኩባያ፡- **ሽማግሌው በኩባያ ውሃ ጠጡ፡፡**

፪.ድስት፡- **ልጅቷ በሸክላ ድስት ወጥ ሰራች፡፡**

፫. ማንኪያ፡- ........................................ ፮. ሹካ፡- ........................................

፬. ምጣድ፡- ........................................ ፯. ብርጭቆ፡- ........................................

፭. ስኒ፡- ........................................ ፰. ማማሰያ፡- ........................................

# ክፍለ ትምህርት ስምንት

የክፍለ ትምህርቱ **ዓላማ፡-** ከተሰጡ ቃላት ውስጥ ምድብ ቦታቸውን በመለየት ማስቀመጥ፡፡

**ትዕዛዝ ፩.** መምራችሁ ስለተመጣጣኝ ምግብ ጠቀሜታ የሚነግሯችሁን አዳምጡ፡፡

**ትዕዛዝ ፪.** ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላት በየምድባቸው በመዘርዘር ጻፍ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| እንቁላል | ማር | ካሮት |
| አሳ | ዳቦ | ፍራፍሬ |
| ሥጋ | በቆሎ | ሰላጣ |

**መልመጃ** ፡ ከላይ የተጠቀሱትን የምግብ አይነቶች ከሚሰጡት ጥቅም አንፃር በየምድባቸው በዝርዝር ጻፍ፡፡

፩. ሃይልና ሙቀት ሰጪ

፪. ከበሽታ ተከላካይ

፫. ገንቢ

## ክፍለ ትምህርት ዘጠኝ


**የክፍለ ትምህርቱ ዓላማ፡- ተገቢ ሥርዓትን ማወቅ፣**

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፣ ሥዕሎቹን ከመግለጫቸው ጋር ታዛምዳላችሁ፡፡

**ትዕዛዝ ፩.** መምህራችሁ የሚየሰሟችሁን "ጨረቃ ድንቡል ቦቃ" የሚለውን መዝሙር አድምጡ፡፡

**ትዕዛዝ ፪.** ቀጥሎ የቀረቡትን ሥዕሎች ከመግለጫቸው ጋር አዛምዱ፡፡

ሀ. ተማሪዎች የባንዲራ ሥርዓት እያከበሩ ነው፡፡



ለ. ርዕሰ መምህር/ት የተጣሉ ተማሪዎችን

አስታረቁ፡፡



ሐ. የጤና ባለሙያዎች በየመንደሩ

የምክር አገልግሎት ሰጡ፡፡



መ. የጽዳት ሰራተኛ አካባቢን አፀዳ፡፡



**መልመጃ**

፩. የባንዲራ ሥርዓት እንዴት ይከበራል፡፡

፪. አካባቢ መቼ ይጸዳል፡፡

፫. ርዕሰ መምህር/ት ምን አደረገ?

# ክፍለ ትምህርት አሥር

## የክፍለ ትንህርቱ ዓላማ፡- ፊደላትን በማጣመር ቃላትን መጻፍ፣

ከዚህ ክፍለ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ፊደላትን በማጣመር ቃላት ትጽፋላችሁ፡፡

**ትዕዛዝ ፩.** ከ "ሀ" እስከ "ፐ" ፊደላትን በመጠቀም ቃላትን በመጻፍ ተለማመዱ፡፡

**ትዕዛዝ ፪.**ተማሪዎች በተለያዩ ፊደላት ቃላትን በምሳሌዎች መሥርቱ፡፡

ሀ. ሀገር፡ ሐ. ሐብል ክ. ክብር ለ .ለማ፡ ነ. ነብር

ሱ. ሱፍ፣ ሱሪ ኑ. ኑር፣ ኑሮ፣ ቀኑ ኡ. አስማን፣ ኡመር

ሀብት፡ ማገር፡ ለም፡ ሐብል ፡ ተማሪ፡ ሽቶ

ቀለበት ፡ ቂጣ፡ ቄስ፡ ቆቅ ቀለበት ቸከሎ ቼቼ ፓስታ

**መልመጃ**፡ በተለያዩ ፊደላት ቃላትን መሥርቱ፡፡

__________ __________ __________ ______

__________ __________ __________ ______

__________ __________ __________ ______

__________ __________ __________ ______

__________ __________ __________ ______

## ክፍለ ትምህርት አስራ አንድ

### የክፍለ ትምህርቱ ዓላማ፡- ዓረፍተ ነገር መመሥረት፣

ተማሪዎች፣ ከዚህ ክፍለ ትምህርት በኋላ ቃላትን በመጠቀም ዓረፍተ ነገር ትመሠርታላችሁ።

**ትዕዛዝ ፩.**መምህራችሁ፣ ከመምህሩ/ሯ መምሪያ የሚያነቡላችሁን እንቆቅልሽ አዳምጡ።

| ጠያቂ | ምላሽ |
|---|---|
| - እንቆቅልህ | ምን አውቅልህ |
| - ስሄድ አገኘኋት ስመለስ አጣኋት? | |

**ትዕዛዝ ፪. ተማሪዎች በሚከተሉት ቃላት የተመሠረቱ ዓረፍተ ነገሮችን ተወያዩባቸው።**

ገለፀ፡ አብይ የተሸፈነውን ምስጢር ገለፀ።

ገፈፈ፡ የበሬውን ቆዳ ገፈፈ።

በላ ፡ የበሬ ሥጋ በላ።

ጠጣ፡ ወንድሙ ውሃ ጠጣ።

**መልመጃ፡-** ቀጥሎ በቀረቡት ቃላት በምሳሌው መሠረት ዓረፍተ ነገር ሥሩ።

፩. ነጋዴ፡- ሸምሱ ኀበዝ ነጋዴ ነው። ፬. ቆሻሻ፡- ..........

፪.ኀረሰ፡- .......... ፭. ንፁህ፡- ..........

፫. ፈጣን፡- .......... ፮. አዝጋሚ፡- ..........

# ምዕራፍ ዘጠኝ

## የጓሮ አትክልትና ፍራፍሬ

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፣

- የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ትሰራላችሁ።
- ቁጥሮችን ትጽፋላችሁ።
- የቤተሰባችሁን ሁኔታ በጽሑፍ ታቀርባላችሁ
- ያዳመጣችሁትን ታሪክ ከባለ ታሪኮች ጋር ታዛምዳላችሁ
- አቅጣጫዎችን በመጠቀም ታሳያላችሁ።
- ስለ ሙያ ዓይነቶች ትዘረዝራላችሁ
- ወቅቶችን ትለያላችሁ
- የጎደሉ ቃላትን በተገቢው ቃላት አሟልታችሁ ትጽፋላችሁ
- ዐረፍተ ነገር መሥርታችሁ ታሳያላችሁ።

## ክፍለ ትምህርት አንድ

**የክፍለ ትምህርቱ ዓላማ፡- አዳምጦ መመለስ፣**

ከዚህ ክፍለ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፣ ምንባቡን በማዳመጥ የአትክልትን ጥቅም ትናገራላችሁ፡፡

### የጓሮ አትክልትና ፍራፍሬ

**የጓሮ** አትክልትና ፍራፍሬ ለምግብነት ይውላሉ፡፡ እንዳንዶቹ ቅጠላቸው ይበላል፡፡ ሌሎቹ ሥራቸው ይበላል፡፡ የተቀሩት ደግሞ ፍሬያቸው ይበላል፡፡ ቅጠላቸው የሚበሉት የአበሻ ጎመን፣ ጥቅል ጎመን፣ አበባ ጎመንና ቆስጣ ናቸው፡፡

*ፍሬያቸው የሚበሉት የጓሮ አትክልት ምን ምን ይመስሏችኋል?*

ፍሬያቸው የሚበሉት ብርቱካን፣ ሙዝ፣ ምንጎ፣ ፓፓያ፣ መንደሪን፣ ሃባብና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ አትክልትና ፍራፍሬዎች ብዙ ጥቅሞችን ይሰጣሉ፡፡ ከበሽታ ይከላከላሉ፣ ተሸጠውም ገንዘብ ያስገኛሉ፤ ንፁህ አየርንም ለሰው ልጅ ይሰጣሉ፡፡ ሲያዩዋቸው ደግሞ ውበት ስላላቸው የመንፈስ እርካታን ይሰጣሉ፡፡ አትክልትና ፍራፍሬዎችን ለማምረት ብዙ ቦታ አይጠይቅም፡፡ ሁሉም ሰው በጓሮው ባለው ትንሽ መሬት ወይም በእቃ ላይ አፈር በመሙላት ማብቀልና መጠቀም ይቻላል፡፡

**መልመጃ፡-** ምንባቡን መሠረት በማድረግ የቀረቡት ጥያቄዎችን መልሱ፡፡

፩. አትክልትና ፍራፍሬ ለምን ጥቅም ይውላሉ፡፡.................................

፪.ፍሬያቸው የሚበሉ የጓሮ አትክልት የትኞቹ ናቸው?............................

፫. የፍራፍሬ ዘሮችን ዘርዝሩ፡፡..................................................................

## ክፍለ ትምህርት ሁለት

**የዕለቱ ትምህርት ዓላማ፡-** አጭር ምንባብ ማንበብ፣

ከዚህ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች አጭር ምንባብ ታነባላችሁ፡፡

**ትዕዛዝ ፩.** የትኛውን የምግብ ዓይነት ትወዳላችሁ? በጓሮአችሁ ምን አይነት አትክልት ወይም ፍራፍሬ እንዳለ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሩ፡፡

**ትዕዛዝ ፪.** ተማሪዎች እኔ ማን ነኝ የሚለውን ምንባብ አንብቡ፡፡

### እኔ ማን ነኝ?

ከፍራፍሬዎች እመደባለሁ፤ ቅርፄ ክብ ነው፡፡ ለመበላት ስደርስ መልኬ ወደ ቢጫ ያደላል፤ ተልጬም እበላለሁ፡፡ በውስጤ ከስምንት እስከ አሥር የሚደርሱ ክፍሎች አሉኝ፡፡ በየክፍሎቼ ውስጥ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ፍሬዎች አሉኝ፡፡ ሰዎች ሲመገቡኝ በጣም የምጣፍጥና ጤና የምሰጥ ነኝ፡፡ እኔ ማነኝ?

**መልመጃ፡-**

ከዚህ በታች በተሰጠው ምሣሌ መስረት ዓረፍተ ነገር ፃፉ፡፡

ምሳሌ፡- ዘር - ጤፍ ተዘራ፡፡

፩. ሙዝ

፪. ቅጠል

፫. ቆስጣ

፬. ሰላጣ

፭. ቀይሥር

# ክፍለ ትምህርት ሦስት

## ድርጊቶችን በቅደም ተከተል መጻፍ

**ተማሪዎች ከዚህ ክፍለ ትምህርት በኋላ፡- ድርጊቶችን በቅደም ተከተል ታስቀምጣላችሁ፡፡**

**ትዕዛዝ፡-** ተማሪዎች በመምህራችሁ በሚሰጣችሁ ትዕዛዝ መሠረት ሐሳባችሁን ግለጹ፡፡

**ምሳሌ፡-** → ሰው → ይወለዳል → ያድጋል → ይሞታል

**መልመጃ፡-**

**ሀ.** በምሳሌው መሠረት የሚከተሉትን ድርጊቶች በቅደም ተከተል ጻፉ፡፡

| | |
|---|---|
| ፩. ቁርስ መብላት | ፪. ፊትን መታጠብ |
| ፫.እጅን በውሃና ሳሙና መታመብ | ፬. በጠዋት መነሣት |
| ፭. ወደ መጸዳጃ ቤት መሔድ | |

**ለ.** ብርቱካንን ለመመገብ ቅደም ተከተሉን በምሰሌ ካየን፣ ድንችን ምን ማድረግ አለብን?

**ብርቱካን፡-** → ይገዛል → ይታጠባል → ይላጣል → ይበላል

**ድንች፡-** → ☐ → ☐ → ☐ → ☐

## ክፍለ ትምህርት አራት

**የትምህርቱ ዓላማ፡- ቁጥሮችን መጻፍ**

**ተማሪዎች ከዚህ ክፍለ ትምህርት በኋላ፣ ቁጥሮችን ወደ ፊደል ትቀይራላችሁ፡፡**

**ትዕዛዝ፡-ተማሪዎች በአሀዝ የቀረቡ ቁጥሮችን ወደ ፊደል ቀይሩ፡፡**

**ምሳሌ፡-**፩ (፩) አንድ 2 (፪) ሁለት

| | | | |
|---|---|---|---|
| 3 (፫) | ________ | 10 (፲) | ________ |
| 4 (፬) | ________ | 20 (፳) | ________ |
| 5 (፭) | ________ | 30 (፴) | ________ |
| 6 (፮) | ________ | 40. (፵) | ________ |
| 7 (፯) | ________ | 50 (፶) | ________ |
| 8 (፰) | ________ | 60 (፷) | ________ |
| 9 (፱) | | 70 (፸) | ________ |
| | | 80 (፹) | ________ |
| | | 90 (፺) | ________ |
| | | 100 (፻) | |

# ክፍለ ትምህርት አምስት

## የክፍለ ትምህርቱ ዓላማ፡-የቤተሰብን ሁኔታ መጠያየቅ

**ተማሪዎች ከዚህ ክፍለ ትምህርት በኋላ፣ ራሳችሁንና ቤተሰባችሁን ታስተዋውቃላችሁ፡፡**

**ትዕዛዝ፡-**ተማሪዎች በጥንድ ጥንድ ሆናችሁ ስለ የቤተሰባችሁ ሁኔታ ተነጋገሩ፡፡

ተማሪ ፩. ስምህ ማነው

ተማሪ ፪ መጩ

ተማሪ ፩. ያባትህስ

ተማሪ ፪.ሽኩር

ተማሪ ፩. ስንት ወንድሞች አሉህ?

ተማሪ ፪. ሦስት ወንድሞች አሉኝ፡፡

ተማሪ ፩. እህቶችስ?

ተማሪ ፪. እህቶቼ ሁለት ናቸው፡፡

ተማሪ ፩. አመሰግናለሁ፡፡

ከላይ ባየነው ምልልስ መሠረት ሁላችሁም የቤተሰቦቻችሁን ሁኔታ በመጠያየቅ ውጤቱን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

# ክፍለ ትምህርት ስድስት

**የክፍለ ትምህርቱ ዓላማ፡- አንብቦ መረዳት፣**

**ተማሪዎች ከዚህ ክፍለ ትምህርት በኋላ፡- ከምንባብ የሚወጡ ጥያቄዎችን ትመልሳላችሁ፡፡**

**ትዕዛዝ ፩.** ተማሪዎች አለመማር የሚያስከትለውን ችግር ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

**ትዕዛዝ፪.** "ወይ አለማወቅ" የሚለውን ምባብ አዳምጡ፡፡

**ወይ አለማወቅ**

"ተረኛ" ተረኛ" አለ ነርሱ፡፡ ወይዘሮ አልማዝ "አቤት!" ብለው የሁለት ዓመት ልጃቸውን ይዘው ገቡ፡፡

"ምኑን ነው ያመመው?" ዶክተር ጠየቁ፡፡ "እያዩትም ፀጉሩ ሳስቷል፤ ሆዱ ተነፍቷል፤ ድዱም ይደማል፡፡" አሉ ወ/ሮ አልማዝ፡፡ ዶክተርም "በጣም ያሳዝናል! እንደዚህ ያደረገው የተመጣጠነ ምግብ ያለማግኘቱ ነው፡፡ አሁንም ወተት፣ እንቁላል፣ ማር፣ አትክልትና ፍራፍሬ ይመግቡት፤ ቶሎ ይሻለዋል፡፡ ለአሁኑ ግን መድሃኒት አዝዝለታለሁ፡፡" በማለት አስረዳቸው፡፡ ወ/ሮ አልማዝም "ወይ አለማወቅ! ልጄን በምግብ እጥረት ገድዬው ነበር፡፡" ብለው አለቀሱ፡፡

*(ምንጭ ከመሳይ ለማ፣ የመጽሐፍ አዘጋጅ)*

**መልመጃ.** ከምንባቡ የተውጣጡ ጥያቄዎችን መልሱ፡፡


| | |
|---|---|
| ፩. "ተረኛ" ተረኛ" ያለው ማነው?<br>፪. ዶክተሩ ምን ጠየቁ?<br>፫. ወይዘሮ አልማዝ ምን ብለው መለሱ? | ፬. ዶክተሩስ ፡ችግሩን ሲያስረዱ ምን አሉ ምንስ ምክር ሰጡ?<br>፭. በመጨረሻም ወ/ሮ አልማዝ ለምን አለቀሱ? |

# ክፍለ ትምህርት ሰባት

**የክፍለ ትምህርቱ ዓላማ፡- አቅጣጫን መጠቆም፣**

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ አቅጣጫዎችን እና አቅጣጫ ጠቋሚ የሆኑ ቃላትን ታውቃላችሁ፡፡

**ትዕዛዝ፡-** በሥዕሉ ላይ የተጠቀሱትን ቦታዎች አመልክቱ፡፡

| | | |
|---|---|---|
|  | **መንገድ** |  |
|  | |  |

**መልመጃ**

**በሥዕሉ ላይ የተጠቀሱትን ቦታዎች አመልክቱ፡፡**

**፩. ት/ቤቱ ያለው ከመንገዱ ………….ነው፡፡**

**ሀ, በግራ ለ, በቀኝ ነው**

**፪. ቤተክርስቲኑ ያለው ከት/ቤቱ በ ---------- በኩል ነው**

**፫. ሱቁ ያለው ከመስጊዱ ----------- ነው**

**፬. መስጊዱ ያለው ከመንገዱ በ -------- በኩል ነው**


## ክፍለ ትምህርት ስምንት

**የክፍለ ትምህርቱ ዓላማ፡- የተግባራት ቃላትን ማወቅ፣**

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ ስለ ሙያ ዓይነቶች ትዘረዝራላችሁ፡፡

**ትዕዛዝ ፩.** ስለምታውቋቸው የሙያ ዓይነቶች ተናገሩ፡፡

**ትዕዛዝ ፪.** የሚከተሉትን ሥዕሎች ሙያን ከሚገልጹ ቃላት ጋር አዛምዱ፡፡

| " ሀ " | | " ለ " |
|---|---|---|
| ፩. |  | ሀ. ገበሬ |
| ፪ |  | ለ.ዶክተር |
| ፫. |  | |
| ፬. |  | ሐ. መምህር/ት |
| ፭. |  | መ. ፖሊስ |

## ሠ. ባንባ ሠራተኛ

**<u>መልመጃ</u>**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡

፩. የፖሊስ ተግባር ምንድነው?

፪.የመ/ር ተግባር ምንድነው?

፫. ሀኪም ተግባር ምንድነው?

፬. የባንባ ሠራተኛ ተግባር ምንድነው?

፭. የገበሬ ተግባር ምንድነው?

# ክፍለ ትምህርት ዘጠኝ

## አያያዥ ቃላትን ማውጣት

**የዕለቱ ትምህርት ዓላማ፣ ቃላትን ከምንባብ ማውጣት፣**

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፣ አያያዥና ወቅቶችን ገላጭ የሆኑ ቃላትን ትለያላችሁ፡፡

**ትዕዛዝ ፩.** ተማሪዎች ስለ አመቱ ወቅቶች ተናገሩ፡ እህል መቼ ይዘራል? መቼ ይታጨዳል? መሬት መቼ ይታረሳል?

**ትዕዛዝ ፪.** ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ በጥሞና በማንበብ አያያዥ ቃላት ለይታችሁ አውጡ፡፡

**የዓመቱ ወቅቶች**

አንድ አመት አራት ወቅቶች አሉት፡፡ **እነሱም** በጋ፣ በልግ፣ ክረምት እና ፀዳይ በመባል ይታወቃሉ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ታህሳስ፣ ጥር፣ የካቲት የበጋ ወቅት ናቸው፡፡

የበልግ ወቅቶች ደግሞ መጋቢት፣ ሚያዚያ እና ግንቦት ሲሆኑ የክረምት ወቅቶች ደግሞ ሰኔ፣ ሐሙሌ እና ነሀሴ ናቸው፡፡ ሌሎች ደግሞ መስከረም፣ ጥቅምት እና ሕዳር የፀደይ ወቅት ይባላሉ፡፡

## መልመጃ፡-

ሀ. ከምንባቡ ውስጥ አያያዥ ቃላትን የያዙ ዓረፍተ ነገሮችን ለይታችሁ አውጡ።


፩. የበጋ ወቅቶች፡- ታህሳስ --------------

፪. የክረምት ወቅት፡- ሰኔ ----————


፫. የበልግ ወቅት፡- መጋቢት -------------

፬. የፀደይ ወቅት፡- መስከረም ————

ለ.ከታች የቀረቡትን በዶ ቦታዎች በተገቢው ቃላት አሟሉ፡፡



ሐ. ከላይ በተመራችሁት መሠረት በባዶ ቦታዎች ያልተሟሉ ቃላትን አሟሉ።



## ክፍለ ትምህርት አሥር

**የዕለቱ ትምህርት ዓላማ ዓረፍተ ነገር መመሥረት፣**

**ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፣ ነጠላ ዓረፍተ ነገር ትመሠርታላችሁ።**

**ትዕዛዝ.**

ከታች በቀረቡት ቃላት የተመሰረቱትን ነጠላ ዓረፍተ ነገሮች ጻፉና ደጋግማችሁ አንብቧቸው።

፩. አጠበች፡- ኡሚ ልብስ አጠበች።

፪. መደበች፡- ከበቡሽ ሽንኩርት መደበች።

፫. ጀመረች፡- ሄሊሴ ትምህርት ጀመረች።

፬. ተከለች፡- አለሚቱ ማንጎ ተከለች።

፭. አወጣች፡- ነፃነት ድስቱን አወጣች።

**መልመጃ፡-** በምሳሌው መሠረት በተሠጡት ቃላት ሌሎች ዐረፍተ ነገሮችን ሥሩ።

**ምሳሌ፡-** ጨለመ፡ ዛሬ ቀኑ ቶሎ ጨለመ።

ዘነበ፡ ዝናቡ ዘነበ።

ሀ. ሄደ ፡ ..........................................

ለ. አበረረ ፡ ..........................................

ሐ. ነገረ ፡ ..........................................

# ምዕራፍ አሥር

## ተላላፊ በሽታዎች

**ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ፡-**

- ታሪክን በማዳመጥ ጥያቄዎችን ትመልሳላችሁ፡፡
- ቃላትን በማጣመር ሀረጋትንት ትመሰርታላችሁ፡፡
- ሁነቶችን በቅደም ተከተል በማስተካከል ታስቀምጣላችሁ፡፡
- ራሳችሁን የሚገልጽ ጽሁፍ ታዘጋጃላችሁ፡፡
- አንደኛ መደብ፣ ነጠላና ብዙ ተውላጠ ስሞችን ትለያላችሁ፡፡
- በቀረቡት ቃላት ዓረፍተ ነገሮችን ትመሰርታላችሁ፡፡

## ክፍለ ትምህርት አንድ

**የክፍለ ትምህርቱ ዓላማ፡- መናገር፣**

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፣ በሽታን የመከላከል ዘዴን ትናገራላችሁ።

"በሽታን መከላከል"

በንጽህና ጉድለት የሚመጡ በሽታዎችን መከላከል ይቻላል። ለምሳሌ ጸጉርን፣ ገላን እና እጅን በመታጠብ ፣ ልብስን በማጠብ የተስቦ በሽታን እንከላከላለን። ቆሻሻን ሰብስቦ በማቃጠልና ዓይነ ምድርን በመጸዳጃ ቤት በመጠቀም ደግሞ ተቅማጥን፣ የዓይን ማዝንና ጉንፋንን መከላከል ይቻላል። በክረምት የሚያቁሩ ኩሬዎችን በማድረቅ እና የወባ ትንኝ እንዳትራባ በማድረግም የወባ በሽታን መቀነስ ይቻላል።

**መልመጃ**

በምንባቡ መሠረት ጥያቄዎችን ሥሩ።

ሀ. የተስቦ በሽታን እንዴት መከላከል ይቻላል?

ለ. የተቅማጥ፣ የዓይን ማዝና የጉንፋን በሽታን ለመከላከል ምን ማድረግ ይገባል?

ሐ. የወባ ትንኝ እንዴት ትራባለች?

## ክፍለ ትምህርት ሁለት

## የሐረግ ምስረታ

**የክፍለ ትምህርቱ ዓላማ፡- ሀረጋትን መመሥረት**

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ቃላትን በማጣመር ሀረጋትን ትመሠርታላችሁ፡፡

**ትዕዛዝ ፡-**ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላት ከ"ቤት" ጋር አጣምሩ፡፡

| ቃላት | ምሳሌ | ሐረግ |
|---|---|---|
| ማረሚያ | ቤት | የማረሚያ ቤት |
| ማዕድ | | |
| ዳቦ | | |
| ሥጋ | | |
| ምግብ | | |

ማስታዎሻ

ሀረግ ማለት ትርጉም ያላቸው ሁለትና ከዚያ በላይ ቃላት ተቀናጅተው የሚፈጥሩት መዋቅር ሲሆን "ሀረግ" የሚለውን ስያሜ ሊያገኝ የቻው አግባብነት ያላቸው ቃላት ተያይዘው በመርዘም ሀረግ ስለሚያስመስሉት ነው፡፡

፩. ቆንጆት ወዴት ፫. የመኪና ማቆሚያ

፪. መምህሩ በመጨረሻ ፬. የትራፊክ መብራት

**መልመጃ**፡- ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላት በማጣመር ሐረግ መሥርቱ፡፡

ሀ. መኪና ------------ ተራ

ለ. ለመሄድ ----------- ወጣ

ሐ. ሞተረኛ ----------- ልጅ

መ. ቀዩ ---------------- አስተናጋጅ

## ክፍለ ትምህርት ሦስት

**የክፍለ ትምህርቱ ዓላማ፡- ሁነቶችን ቅደም ተከተል ማስያዝ፣**

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ያዳመጣችሁትን ታሪክ በቅደም ተከተል ታስቀምጣላችሁ፡፡

**ትዕዛዝ.** ተማሪዎች ባለፈው ክፍለ ጊዜ ስለምን እንደተማራችሁ ተናገሩ፡፡

**መልመጃ.**

ቀጥሎ የተዘበራረቁ ዐ.ነገሮች ቀርበዋል፡፡ መምህራችሁ ከመምህር/ት መምሪያ ሲያነቡ ሁነቱን በማስተካከል አስቀምጡ፡፡

፩. ዋሽንቱን ወደ በሬው ወረወረ፡፡

፪. በድንገት አንድ በሬ በቆሎ ማሳ ገባበት፡፡

፫. እረኛው ቢሮጥ አልደርስበት አለ፡፡

፬. ከብቶቹን አሰማራና ዋሽንቱን መንፋት ጀመረ፡፡

፭. ከዕለታት አንድ ቀን እረኛው በጠዋት ተነሳ፡፡

፮. ከብቶቹን እየነዳ ወደ ተከለለላቸው የግጦሽ ቦታ ሄደ፡፡

፯. ዋሽንቱን ያዘ፡፡

የተሰጠውን ጅምር ምሳሌ መሠረት በማድረግ አስተካክሉ፡፡

ምሳሌ፡- ፩፡ ከእለታት አንድ ቀን እረኛው በጠዋት ተነሳ

፪፡ ዋሽንቱን ያዘ

፫. ____________ ፬.____________ ፭. ____________ ፮. ____________

፯.____________

## ክፍለ ትምህርት አራት

**የክፍለ ትምህርቱ ዓላማ፡- የሥርዓተ ነጥብን አጠቃቀም ማወቅ፣**

**ትዕዛዝ** ተማሪዎች ባለፈው ትምህርት የተማራችሁትን አስታውሱ፤ የሁለት ነጥብ፣ የነጠላ ሰረዝና የአራት ነጥብን አገልግሎት ተናገሩ፡፡

**ትዕዛዝ** ተማሪዎች! ቀጥሎ በቀረቡት ዐ.ነገሮች ዙሪያ ተወያዩ፡፡

ሀ. ከየት መጣህ?

ለ. በምን መጣህ?

ሐ. ከእናንተ በትምህርት ጎበዝ ማነው?

መ. የቤተሰብ ምጣኔ ማለት ምን ማለት ነው?

**መልመጃ**

ትእዛዝ፡- ቀጥሎ በተሰጡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የጎደለውን

ሥርዓተ ነጥብ በተገቢው ቦታ አስገቡ፡፡

ሀ. አቶ ገመዳ ቤታቸው በጣም ንጹህ ነው ግቢያቸውም ንጹህና በአበቦች ያጌጠ ነው አቶ ገመዳ በግቢያቸው ዙሪያ ጥሩ ጥሩ ዛፎችን ተክለዋል

ለ. አባትህ ለበአል ምን ገዙልህ

ሐ. ደንድር ከድር ዋሚሻና ደራሬ ወላጆቻቸውን ይረዳሉ

መ. ንጹህ አየር ለሰው ልጅ አስፈላጊ ነው

ሠ. ታላላቅ ወንድሞቼ አበበ ፈቀደ በለጠና መንግስቱ ናቸው

## ክፍለ ትምህርት አምስት

**የክፍለ ትምህርቱ ዓላማ፡- ተውላጠ ስሞችን መለየት፣**

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፣ ነጠላና ብዙ ተውላጠ ስሞችን ትለያላችሁ።

**ተውላጠ ስሞች፡-**

**አብዛኛውን ጊዜ ሰዋስዋዊነትን ለማመልከት የሰውን (የሰዎችን) ስም ላለመጥቀስ ሲያስፈልግ በተተኪነት የምንጠቀምባቸው ናቸው። እነሱም በመደብ፤ በቁጥር እና በጾታ ይለያያሉ።**

<table>
<tr><td>መደብ</td><td>ቁጥር</td><td></td></tr>
<tr><td></td><td>ነጠላ</td><td>ብዙ</td></tr>
<tr><td>፩ኛ</td><td>እኔ</td><td>እኛ</td></tr>
<tr><td>፪ኛ</td><td>አንተ</td><td rowspan="3">እናንተ</td></tr>
<tr><td></td><td>አንቺ</td></tr>
<tr><td></td><td>እርስዎ</td></tr>
</table>

**መልመጃ፡-**

በምሳሌው መሠረት ዓረፍተ ነገር ሥሩ።

እኔ እና እሱ ቀድመን መጣን።

ሀ. እኔ የሚለው የስም ምትክ ስንተኛ መደብ ነው?

ለ. አንተ የሚለው ተውላጠ ስም የትኛውን መደብ ያመለክታል? ጾታውስ?

# ክፍለ ትምህርት ስድስት

## የክፍለ ትምህርቱ ዓላማ ማዳመጥና መናገር፣

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች ከምንባቡ የሚወጡትን ጥያቄዎች ትመለሳላችሁ፡፡

**ትዕዛዝ.** መምህራችሁን በመከተል መዝሙሩን ዘምሩ፡፡

**ቀይዋ ወፍ ቀይዋ ወፍ በመስኮቴ ገባች፣**
**ቀይዋ ወፍ ቀይዋ ወፍ በመስኮቴ ገባች፣**
**ቀይዋ ወፍ ቀይዋ ወፍ በመስኮቴ ገባች፣**
**ቀይዋ ወፍ ቀይዋ ወፍ በመስኮቴ ወጣች**
**ውይ! በራ ሄደች፣ ውይ! በራ ሄደች፣ ውይ! በራ ሄደች፣**

### ፍትህ ምንድን ነው?

ፍትህ ማለት አለማዳላት ማለት ነው፣ እውነትን መናገር ነው፡፡ እውነትን መሠረት አድርጎ መስራት ነው፡፡ ፍትህ በትምህርት ቤት፣ በቀበሌና በቤተሰባዊ ኑሮ ውስጥ አስፈላጊ ነው፡፡ ፍትህ የሰዎች ህይወትና ኑሮ ጥሩ እንዲሆን ያደርጋል፡፡ በሰዎች መካከል ምንም አይነት ልዩነትና አድሎ እንዳይፈጠር ይጠቅማል፡፡ በጓደኝነትም ደረጃ አንዱ የበላይ ሌላው የበታች እንዳይሆን በማድረግ የሰዎችን መብት ያስከብራል፡፡ (ሥነ ዜጋ ት/ት ክፍል 2003 ዓ.ም)

**መልመጃ.**

ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ሥሩ፡፡

፩. ፍትህ ምን አስተዋጽኦ አለው? --------------------

፪. ፍትህ በሰዎች ህይወት ምን ሚናው ምንድነው? ---------

፫. ፍትህ ለጓደኝነት ምን አስተዋጽኦ አለው? --------------

## ክፍለ ትምህርት ሰባት

**የክፍለ ትምህርቱ ዓላማ ዓረፍተ ነገር መመሥረት፣**

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች የነጠላ ዓረፍተ ነገር ምንነት ለዩ፣

**ትዕዛዝ ፩.**

ተማሪዎች በየተራ እየተነሳችሁ በቃላችሁ ዐረፍተ ነገር መሥርቱ፡፡

ማስታወሻ

ዓረፍተ ነገር የነገር መቋጫ ወይም ማረፊያ ማለት ነው፡፡ ነጠላ ዓረፍተ ነገር አንድ ሀሳብ ብቻ የያዘ ሲሆን በሦስት የተለያዩ መልኮች ሊከሰት ይችላል፡፡

ሀ. ሐተታዊ (ተራ) ዓረፍተ ነገር፡፡ ምሳሌ፡- ታፈሰ ሳር አጨደ፡፡

ለ. ጥያቄያዊ ዓረፍተ ነገር፡፡ ምሳሌ፡- ዕድሜህ ስንት ነው?

ሐ. ትዕዛዛዊ ዓረፍተ ነገር፡፡ ምሳሌ፡- ከጓኛህ ጋር አጥና!

(ባዬ 2000)

**መልመጃ**

ቀጥሎ በቀረቡት ቃላት ዓረፍተ ነገር መሥርቱ፡፡

ሀ. በላ ----------------------

ለ. ጎበዝ --------------------

ሐ. ግባ -----------------------

## ክፍለ ትምህርት ስምንት

**የክፍለ ትምህርቱ ዓላማ፡- መጻፍ**

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች እራሳችሁን የሚገልጽ ጽሁፍ ትጽፋላችሁ፡፡

**መልመጃ**

ሀ. ተማሪዎች እራሳችሁን የሚገልጽ ዓረፍተ ነገር ጻፉ፡፡

ሙሉ ስም ----------------------- የትውልድ ቦታ ------------

የክፍል ደረጃ ------------------ የቤተሰብ ብዛት----------------

የሚወዱት ምግብ ---------------------- የቤተሰብ ስራ ------
----------

ለ. ተማሪዎች ከላይ የጻፋችሁትን ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

> ምሳሌ፡- መለሰ መጨ ያዩ የተወለድኩት በሀዲያ ዞን፣ ምስራቅ ባደዋቾ ወረዳ፣ ዌራ ቀበሌ ነው፡፡ አሁን የ፫ተኛ ክፍል ተማሪ ነኝ፡፡ የምኖረው ከቤተ ሰቦቼ ጋር ነው፡፡ የምወደው ምግብ ቆጮ በጎመን ሲሆን ቤተሰቦቼ አርሶ አደሮች ናቸው፡፡

ሐ. የመለሰ መጨን አገላለጽ ምሳሌ በማድረግ ባለ አምስት ዐረፍተ ነገር ጽሑፍ ጻፉና ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡ ለጓደኞቻችሁም ድምጻችሁን ከፍ አድርጋችሁ አንብቡላቸው፡፡

.

## ዋቢ ጽሑፎች


መሥፍን ልሳኑ። (1952)። የአማርኛ መጽሔተ ቃላት። አዲስ አበባ፣ አርትስቲክ ማተሚያ ቤት።

ባየ ይማም። (2000)። የአማርኛ ሰዋስው። አዲስ አበባ፣ እሌኒ ማተሚያ ቤት።

ትምህርት ምኒስቴር። (2009)። አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ የመምህር መምሪያ።

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ። (1934)። መዝገበ ፊደል። አዲስ አበባ፣ አርትስቲክ ማተሚያ ቤት።

ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ት/ቢ። (2009)። አማርኛ እንደ ሁለተኛ መፍቻ ቋንቋ የተማሪ መጽሐፍ

ገብሩ ደስታ። (1915) ። ያማርኛ ሰዋስው መሪ። አዲስ አበባ፣ ራስ ተፈሪ ማተሚያ ቤት።